በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ላይ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ነሐሴ/2005

ማውጫ ገጽ

ክፍል አንድ

መግቢያ 1
የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፋይናንስ ምንጭ 3
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን 4
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራዕይ፣ ዓላማዎች እና ኃላፊነት 4
የአሠራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION) 6
የኦዲቱ ዓላማ 8
የኦዲቱ አከባቢ 8
የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ 8
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 9
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴዎች 9

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች 10
የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን አግባብ ባለው ደረሰኝ የሚሰበስቡ መሆኑን በተመለከተ 11
የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ በመ/ቤቱ ስም በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ ባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን በተመለከተ 14
የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብን አስመልክቶ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ 16
የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዳዲስ ዋጋ እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በተመለከተ 17
የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ 19
የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ 20
የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያገኙትን አስፈቅደው የሚጠቀሙ መሆኑን እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች የግዥ መመሪያ እና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው መፈጸሙን በተመለከተ 21
የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢያ ጥናት ላይ የተመሠረተ ግዥ መፈጸማቸውን በተመለከተ 23

የዩኒቨርሲቲዎቹ የገቢ ማመንጫ ተቋማት አደረጃጀትን በተመለከተ 24

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን የሚያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ............................ 25

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ.. 27

በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡና የሙያ ሥነ ምግባር የሚያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ 30

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን በተመለከተ................ 31

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማቅረባቸውን በተመለከተ 34

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ሃሳቦች 36

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች 42

አባሪ 1- የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች- I

አባሪ 2፡- የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ ስለአሳተሟቸው ደረሰኞች...............................v

አባሪ 3፡-ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈቃድ ውጭ ስለተከፈቱ የባንክ ቁጥሮች.........................vii

አባሪ 4፡- የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የሰበሰቡትን የዕለት ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ስለማድረጋቸው...x

አባሪ 5፡- ለውስጥ ገቢ የፀደቀ በጀት እና አፈፃፀም xii

አባሪ 6፡- ስለ ቁጥ ቁጥ ግኝ xiii

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማቀላጠፍ እንዲሁም ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በአግባቡ ለማከናወን ይረዳ ዘንድ መንግሥት በ2002 በጀት ዓመት 76,394,916,748.71 እና በ2003 በጀት ዓመት 102,872,227,741.49 ብር ከመደበኛ ገቢ፣ ከውጪ እርዳታ፣ ከካፒታል ገቢ፣ ከውጪ ብድር እና ከአገር ውስጥ ብድር የተሰበሰበ መሆኑን ዓመታዊ የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ያመለክታል፡፡

2. የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመማር ማስተማር ዓላማቸውን ለማሳካት የውስጥ ገቢ የሚሰበስቡ ሲሆን ይህም ከመማር ማስተማር፣ ከማማከር፣ ከኪራይ፣ የዕንግዳ ማረፊያ፣ ከእንጨትና ብረታብረት ኮንስትራክሽን፣ ከግብርና ምርት ውጤቶች፣ ከጤና ተቋማት፣ ከእደ ጥበብና ወርክ ሾፖች፣ ከመዝናኛ ክበባት፣ ከማህበረሰብ ት/ቤት እና ከፕሮጀክት ፋይናንስ አገልግሎቶች ነው፡፡

3. የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተቋም ነፃነትና ለመንግሥትና ሕዝብ ጥቅም አጠቃላይ ባለው ተጠያቂነት መካከል ተገቢው ሚዛን እንዲጠበቅ፤ እንዲሁም በአገሪቱ የዕድገት ፍላጐት ላይ የተመሠረተ የማህበረሰብና የማማከር አገልግሎትን እንዲያበረክትና ተቋማዊ ነፃነትን ከተጠቃሚነት ጋር ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 650/2001 ወጥቷል፡፡

4. በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 190/2002 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ገቢውን ያገኘው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በገቢው መጠቀም ካልተፈቀደለት በስተቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥትን ንብረት በማስወገድ ያገኘውን ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

5. የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዓላማው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም የሚያስችል የፋይናንስ አዋጅ 648/2001፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 190/2002 እና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ 650/2001 መሰረት ያደረገ ወጥ የሆነ መመሪያ እንዲዘጋጅ በመርዳት ሀገሪቷ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምትመድበው በጀት በአግባቡ ለታቀደለትና ለታለመለት አላማ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

6. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየዓመቱ የሚያገኙትን የውስጥ ገቢያቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በሪፖርት ማሳወቅ ያለባቸው መሆኑንና በበጀት አፀድቀው በዕቅድ ለያዙዋቸው ሥራ ብቻ ማዋል ያለባቸው መሆኑን የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 650/2001 ይገልፃል፡፡

7. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 11 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ረገድ የፌደራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አቅም የመገንባት ተግባር ያከናውናል፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በኃላፊነቱ ሥር የሚገኝ የመንግሥት ሀብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን እና ውጤታማነትን ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈፀሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

8. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ሥርዓታቸው የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 190/2002፤ የተለያዩ የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ እንዲሁም ለአጠቃቀም የመንግሥት ግዥ መመሪያዎች የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡

9. ስለሆነም ሚኒስቴር መ/ቤቱና የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው የተሰጣቸውን

ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት ተገቢው የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረጋቸውንና እንዲሁም የተዘረጋው ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

10. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት እና ተቋማቱ ከውስጥ ገቢያቸው ሰብስበው ከሚያፀድቁት በጀት የሚመደብ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩት የአዲስ አበባ፣ የአዳማ እና የባህርዳር ዩኒቨርሲቲዎች የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት በ2003 በጀት ዓመት ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት /መደበኛ በጀት/ በድምሩ ብር 2,945,299,369.40 ከውስጥ ገቢ በጀት በድምሩ ብር 62,154.400.00 በጠቅላላ ብር 3,007,453,769.40 የተመደበላቸው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በዚሁ በጀት ዓመት ብር 2,574,457,798.5 ሥራ ላይ ያዋሉ መሆኑን ከመንግሥት ዓመታዊ ሂሣብ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣንና ኃላፊነት

11. ገንዘብና ኢኮኖሚ ለማት ሚ/ር ከተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነት መካከል ከኦዲቱ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብለው የተመረጡት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

    1. የፌዴራል መንግሥት ፋይናንስ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣ መከታተል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመንግሥት መ/ቤቶችን የፋይናንስ እንቅስቃሴ ኦዲት ማስደረግ፣
    2. የመንግሥት ሀብት በትክክል ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የዕቅድ አዘገጃጀት፣ የሀብት ድልድል እና የበጀት አመዳደብ ሥርዓት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
    3. የመንግሥት ገንዘብ አሰባሰብና ገቢ አደራረግን የተቀላጠፈ ማድረግ፣
    4. በመንግሥት መ/ቤቶች ስም የተከፈቱትን የባንክ ሂሣቦች በዝርዝር መዝግቦ መያዝ፣
    5. የመንግሥት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ውጤታማ እና ኢኮኖሚያዊ እንዲሆን ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣
    6. በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ረገድ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አቅም የመገንባት ተግባር ማከናወን፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኃላፊነት

12. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነት መካከል ከኦዲቱ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብለው የተመረጡት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

    1. በሀገራዊ የትኩረት አቅጣጫ መሠረት አግባብነት ያላቸው የጥናት፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎትን ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሀገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ማካሄድና ግኝቶቹንም ተገቢ በሆነ አግባብ ማሠራጨት እንደ አስፈላጊነቱም ከአገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት እና

ከሌሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር አካዳሚያዊና የምርምር ፕሮጀክቶችን ማካሄድ፣

2. በአዋጅ እና ተፈፃሚነት ባላቸው የሌሎች ሕጐች ድንጋጌዎች መሠረት ሠራተኞችን መቅጠርና ማስተዳደር፣ የተቋሙን ገንዘብና ንብረትም ማስተዳደር፣
3. በተልዕኮው ላይ በመመሥረት ከኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነቶችን መመስረት፣
4. በአዋጅ መሠረት የውሰጥ ደንቦችና መመሪያዎችን ማውጣትና ማስፈፀም፣
5. የተቋሙን ዕቅድ፣ በጀትና አደረጃጀት ማዘጋጀትና መተግበር፣ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም አዋጅ መሠረት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ማቅረብ፣
5. ፈሰስ የሚደረገውን ሂሣብ ተከታትሎ ማስፈፀም፣
6. አመታዊና የቀደምት ዓመታት የትምህርት ግብአትና ውጤት እንዲሁም የፋይናንስ ገቢና ወጪ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ማሳተም፤
7. የየወሩን የገቢ ዕቅድና ያለፈውን ወር ገቢ አፈፃፀም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ማቅረብ
8. የተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ለመንግሥት ገንዘብ አሰባሰብ ተግባር የተሟላና ብቃት ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መኖሩንና የመንግሥት ገንዘብ በሚገባ መሰብሰቡን ማረጋገጥ፣
9. የመንግሥትን ንብረት ተጠቅመው የሚሰበስቡትን ገቢ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሥራ ላይ ማዋል፣
10. ተቋማቱ በገቢው መጠቀም ካለተፈቀደላቸው በቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለ ፈንድ ውስጥ ገቢ ማድረግ፣

የአሠራር ሥርዓት መግለጫ (System description)

13. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለያዩ አገልግሎቶችን ለሕብረተሰቡ በመስጠት ገቢ የሚያገኙ ሲሆን፣ ይህንን ገቢ ለማመንጨት የመንግሥትን ጊዜ፣ ንብረት፣ የሰው ኃይል እና የተለያዩ ሀብቶችን እንደ ግብዓት ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም የመንግሥት የፋይናንስ አዋጅንና ደንብን እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ በተመለከተው መሠረት መሰብሰብና ጥቅም ላይ ማዋል ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም የአሠራር ስርዓት የመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማቋቋሚያ አዋጅን መሠረት በማድረግ የሚቀረጹ ሲሆን፣ ይህም በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚቋቋሙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የአሠራር ሥርዓታቸውን የቢዝነስ ጥናት በማከናወን የቢዝነስ ዕቅድ አዘጋጅተው ዕቅዱ እንዲፀድቅ ያቀርባሉ፤ ዕቅዱም ከፀደቀ በኋላ በሚፈለገው መስክ ኢንቨስት በማድረግ ምርት ወይም አገልግሎት በመስጠት ገቢ ያስገኛሉ፡፡ እንዲሁም ስለአስገኙት ገቢ የምዝናና የግምገማ ሥርዓት በማከናወን የዚህንም ውጤት በማየት እንደገና ቢዝነሱ እንዲቀጥል ወይም እንዳይቀጥል ያደርጋሉ፡፡ ይህም ከገቢ ማመንጫ ኘሮግራም አኳያ የሚከተለውን ሥዕላዊ መግለጫ ይከተላሉ፡፡



ምንጭ:- ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ጥናት ማንዋል የተወሰደ

የኦዲቱ ዓላማ ፡-

14. የኦዲቱ ዋና ዓላማ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋና የዘረጋውም ሥርዓት ተፈፃሚ መሆኑን፣ እንዲሁም የተመደበላቸው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ ሲሆን፣ በክዋኔ ኦዲቱ የተለዩ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮችን ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሣቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ አካባቢ

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ/Potential Audit Area/ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገምን የሚመለከት ነው፡፡

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ከላይ በተገለጸው የኦዲት ዓላማ ሥር ሶስት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

    1. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ የፌዴራል መንግሥትን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 እና የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ 650/2001 ፣ የፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት ያደረገ መሆኑን ማጣራት፤

    2. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ የሚሰበስቡትን የመንግሥት ሀብት አጠቃቀም ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን፣ እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈፀሙን ማጣራት፤

3. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓትን እና ከውስጥ ገቢ ማመንጫዎቻቸው የሚያገኟቸውን ገቢዎች ሙሉ በሙሉ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያሳውቁ መሆኑን ማጣራት፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 31 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት፣ የፌዴራል ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001፣ የፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002፣ የፌዴራል የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003፣ የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003፣ የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003፣ የፌዴራል መንግሥት ጥሬ ገንዘብ አዘገጃጀትና የወጪ በጀት አሰራር ማንዋል (ገ/ኢ/ል/ሚ/ር) እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸዋል፡፡ መመዘኛ መሰፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር <u>በአባሪ 1</u> ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-

18. የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሲሆን፤ እንዲሁም ለኦዲቱ በናሙና በተመረጡ አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህርዳርና አዳማ ዩኒቨርስቲዎች ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ሶስት በጀት ዓመታት ጊዜ የውስጥ ገቢ አሰባሰባቸው፣ አጠቃቀማቸው እና ቁጥጥር ተገቢው ሥርዓት መኖሩን እና ተፈጻሚ መሆኑ ላይ በማተኮር ነው፡፡ ኦዲቱም የተከናወነው የገንዘብና ኢኮኖማ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤትና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት

ተቋማትን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ- መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክሊስት በማጣራት እና በችግሮቹ ዙሪያ በመወያየት፣ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡ ምንም እንኳ ኦዲቱ የተከናወነው በሀገሪቱ ካሉት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በአራቱ ብቻ ቢሆንም፤ በሌሎቹም ተቋማት ተመሳሳይ ችግሮች ካሉ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና በትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤቶች በኩል ችግሮቹ እና የማሻሻያ ሃሣቦቹ የሚተላለፉ መሆናቸውን በማመን ከገንዘብ ጠቀሜታ (Value for money) አንፃር ሁሉንም ኦዲት ማድረጉ አልተመረጠም፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን አግባብ ባለው ደረሰኝ የሚሰበስቡ መሆኑን በተመለከተ፤

19. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን ሲሰበስቡ፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባሳተመው ወይም ገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንዲታተም በፈቀደው ተከታታይ ቁጥር ባለው ደረሰኝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ገቢውም መሰብሰብ የሚገባው ቋሚ /ተገቢው ዋስትና ባለው/ ሠራተኛ ብቻ ሊሆን እንደሚገባው እና የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠር እና ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲቻል በየዕለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በየቀኑ ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጂ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሥር ከሚገኙ የውስጥ ገቢ ማመንጫ ተቋማት መካከል የዩኒቨርሲቲው ሞዴል ፋርማሲ 1 እና 2፣ ሁለት የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች መዝናኛ ክበባት፣ የዩኒቨርሲቲው መጽሐፍትና ሸቀጣሸቀጥ ማዕከል፣ የዩኒቨርሲቲው የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማመረቻ ኢንተርፕራይዝ፣ የኪቶ ፉርዲሣ ሁለገብ ልማት ድርጅት እና የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ ት/ቤት የገቢ ማመንጫ ተቋማት የገቢ ደረሰኞች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያሳተማቸው ወይም ፈቃድ የሰጣቸው ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የሚጠቀሙባቸውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ የሚያጣራ፣ መዝግቦ የሚይዝና የሚከታተል አካል አለመኖሩ እና ከላይ በተዘረዘሩት የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚሠሩ የገቢ ሰብሳቢዎች የኮንትራት ሠራተኞች መሆናቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝር ሁኔታውም በአባሪ 2 ላይ ተመልክቷል/፡፡

21. በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ የሚሰበሰበው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቢሆንም፣ የደረሰኙን ተከታታይ ቁጥር ጠብቀው የማይጠቀሙ እና በአንድ ኮንትራት ሰራተኛም ገንዘብ የሚሰበሰብ መሆኑን፣ እንዲሁም በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ከ2003 -2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያሳተመውን ደረሰኝ ወይም ገኢ/ል/ሚ/ርን በማስፈቀድ የሚታተመውን ደረሰኝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መሰብሰቢያ ዘዴን ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረጉ ታውቋል፡፡

22. እንደዚሁም በኦዲቱ የውስጥ ገቢ አሰባሰቡ የሪፖርት አደራረግ ሥርዓት ሲታይ፣ በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣በባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠር እና ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲቻል በየዕለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በየቀኑ ሪፖርት እንደማያደርጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ለምን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው ወይም አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ፍቃድ በተሰጣቸው ደረሰኞች ሊጠቀሙ እንዳልቻሉ ለዩኒቨርሲቲዎቹ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረው የውስጥ ገቢ የሚያመነጩ ተቋማት አመሰራረትን ተከትሎ ስለሆነ ገቢ እንዳይባክን ታስቦ የታተመ ስለነበር የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያልተጠየቀ መሆኑንና አሁን ግን ጅምሩ መኖሩን፣ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል ዩኒቨርሲቲው ኮሌጅ በነበረበት ወቅት ደረሰኙን ለማሳተም የተፈቀደበት መረጃ እንዳለ ቢነገርም፣ መረጃውን ማቅረብ ባለመቻሉ በአሁኑ ወቅት ደረሰኙን በመግዛት በመገልገል ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

24. በሌላም በኩል የዩኒቨርሲቲዎቹ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የውስጥ ገቢ ቁጥጥር ስርዓት እና የሪፖርት አቀራረብን አስመልክቶ እንዲሁም የፋይናንስ መመሪያው በሚያዘው መሰረት የውስጥ ገቢ ለምን በቋሚ ሠራተኞች ሊሰበሰብ እንዳልቻለ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢን ለመቆጣጠር የተዘረጋ መዋቅር የሌለ

መሆኑና በአዲሱ አደረጃጀት እንደሚስተካከል ፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ተቋማት በየዕለቱ ሪፖርት እንዲቀርብ ያልተደረገበትና ደረሰኞቹ ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ ክትትል አለመደረጉ ከአደረጃጀት ችግር የመነጨ መሆኑን እና አሁን የገቢ ማመንጫና ኢንቨስትመንት ዳይሬክተር ስለተደራጀ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን፣ በጊዜያዊ ሠራተኞች ገቢ እንዲሰበሰብ የተደረገው በጊዜው የቋሚ ሠራተኞች ቅጥር ታግዶ የነበረ መሆኑን ለወደፊቱ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ የሚመደቡትን ሠራተኞች ግን ልዩ ትኩረት በመስጠት ገንዘብ መሰብሰብ በባንክ እንዲሆን እንደሚደረግ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሥራው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ቁጥር ከተፈቀደው መደብ የሚያንስ በመሆኑ ከሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር መደብ እስኪፈቀድ ድረስ በኮንትራት እየተሰራ መሆኑን፣ እስከ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በየቀኑ ወደ አካውንቱ የሚገባው ገንዘብ ከአስገቢዎች ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ፣ የየቀኑን ሪፖርት ለማድረግ አለመቻሉን ነገር ግን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ብሎክ አካውንት ቢከፍትላቸው ይህንን በቀላሉ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ አሳውቀው በተጨማሪም ግኝቱ ትክክለኛ እና አስተማሪ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአዳማ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ ካለው የገቢ ማመንጫ ብዛት በየዕለቱ ሪፖርት ማዘጋጀት የሚያስቸግራቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. ከላይ በኦዲቱ የታዩት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን አግባብ ባለው ደረሰኝና በተቋሙ ቋሚ ሰራተኛ የማይሰበስቡ፣ የተሰበሰበውን የውስጥ ገቢ ለመቆጣጠር የሚያስችል ቅጾችን በማዘጋጀት አደራጅተው የማያስቀምጡ መሆናቸው እንዲሁም ተከታታይ ቁጥር ያለውን ደረሰኝ አለመጠቀማቸው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓታቸው የላላ በመሆኑ የተሰበሰበው ገቢ፣ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን በትክክል ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ መንግሥት ያወጣውን የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ያልተከተለና ለብልሹ አሰራርም እንዲጋለጡ የሚያደርግ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ ባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን በተመለከተ፤

26. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ሊያደርጉ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

27. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር የሚገኙ 28 የገቢ ማመንጫ ተቋማት፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ 9 የገቢ ማመንጫ ተቋማት፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 7 የገቢ ማመንጫ ተቋማት እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ 22 የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የማያደርጉ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ ገቢ የማያደርጉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. በጅማ እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እውቅና በራሳቸው ስም በተከፈተ የባንክ አካውንት የሚያስቀምጡ ሲሆን፣ በተለይ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር አንድ እና ሁለት፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ ኢንተርፕራይዝ እና የማህበረሰብ ትምህርት ቤት የገቢ ማመንጫዎች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ቁጥር 3 የመንግሥት መ/ቤቶች የባንክ ሂሳብ የሚከፈተው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም እርሱ በሚሰይመው ወይም በሚወክለው ባንክ እንደሚሆን ከተጠቀሰው የአሠራር መመሪያ ውጭ ገቢያቸውን እንደሚያስቀምጡ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 3 ላይ ተገልጿል)፡፡

29. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች በሶስቱ ማለትም (አዲስ አበባ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚሰበስቡትን ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማያደርጉ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ 4 ቀርቧል)፡፡

30. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ዩኒቨርሲቲዎች በገቢ ማመንጫዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር በሚያውቀው የባንክ አካውንት ያልተቀመጠበትን እና በእለቱ ባንክ ገቢ ያልተደረገበትን ምክንያት ለሚመለከታቸው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ በፊት ችግሩ የተፈጸመ መሆኑን ገልጸው ይህንንም ችግር መልክ ለማስያዝ አሁን እየታየ ያለበት ሁኔታ መኖሩን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ አጀማመር ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች አገልግሎት ለመስጠትና ለመማር ማስተማሩ ድጋፍ ለማድረግ ስለሆነና በወቅቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ በተገቢው መልኩ እንዲቀመጥ ታስቦ በአስቸኳይ እንዲከፈቱ የተደረጉ መሆኑን እና በግል ባንክ እንዲቀመጥ የተደረገው ደግሞ የተሻለ ትርፍና አገልግሎት ለማግኘት እንደሆነ እንዲሁም የሚገኘው ገቢ አነስተኛ በመሆኑ ፈሰስ አለመደረጉን ነገር ግን ለወደፊት መስተካከል እንዳለበት፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከተለያየ ቁሳቁስ ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ የተማሪዎች ገንዘብ እንደሆነ እና ለቁጥጥር ያመች ዘንድ በተማሪዎች አገልግሎት አካውንት እንዲከፈት መደረጉን እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በ1986 ዓ.ም እና በ1987 ዓ.ም የተከፈቱ አካውንቶች ስለሆኑ መረጃውን ማግኘት አለመቻሉን፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰበሰበው ገንዘብ በዕለቱ ገቢ የማያደርጉት የትራንስፖርት ችግር በመኖሩ እና በክትትል ማነስ መሆኑን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተሰጣቸውን ግኝት በገንቢነቱ እንደሚቀበሉት እና ለወደፊቱ እንደሚያስተካክሉት፤ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ አንዳንድ ጊዜ ችግር ሲፈጠር በእለቱ የተሰበሰበው ገንዘብ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

31. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ አለማድረጋቸው እንዲሁም የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የሚሰበስቡትን ገንዘብ

በእለቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረጋቸው፣ መመሪያን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ ሥርዓት እንዳይዘረጉ እና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብን አስመልክቶ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፡-</u>

32. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

33. ይሁን እንጂ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለትም (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች) የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ መመሪያዎችን በማስተዋወቅ (awareness)፣ ስልጠና በመስጠት እና ስለውስጥ ገቢ አተገባበር ስርዓት በአካል በመገኘት ሙያዊ እገዛ ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

34. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በውስጥ ገቢ፣ በጀት እና ደረሰኝ አጠቃቀም እንዲሁም አጠቃላይ ሪፖርት አቀራረብ ላይ የኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ስልጠና ለመስጠት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

35. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መንግሥት ያወጣውን የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ቀደም ብሎ ተገቢውን እገዛ አለማድረጉ ተቋማቱ የመንግስትን መመሪያና ደንብን ተከትለው እንዳይሰሩ ከማድረጉም በላይ የውሰጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓታቸው ግልጽነት ያለው ተጠያቂነትን በሚያጠናክር እንዲሁም ኢኮኖሚን፣ ቁጠባን እና ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>**የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዳዲስ ዋጋ እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በተመለከተ፤**</u>

36. በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማጸደቅ አለባቸው፡፡ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማትም አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ አራት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው የማያጸድቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ሳያሳውቁ በራሳቸው የሚያከናውኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

38. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በRef.No. VPGSR/LT 059/08 Date 10 March 2008 ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር አዲስ ክፍያን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሳያቀርቡ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ/ሴኔት የተወሰነ መሆኑ፣ በተመሳሳይ መልኩ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሐምሌ 15/2003 ዓ.ም ደብዳቤ ቁጥር ጅዩ 63/968 የድህረ ምረቃ መረሃ ግብርን አዲስ ክፍያን በተመለከተ በዩኒቨርሲው መወሰኑን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው የሴኔት ስብሰባ በቁጥር 001/2004 ዓ.ም በ05/01/2004 ዓ.ም እና በቁጥር 007/2004 ዓ.ም በ22/06/2004 ዓ.ም የአዲስ የትምህርት ክፍያ ዋጋ ጭማሪ ውሳኔ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያለ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ የተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት ለዩኒቨርሲቲዎቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህን አሰራር አለማወቃቸውን ፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል የተወሰነው ተጋባዥ ሌክቸረሮችን ለማግኘት ሲባል አስቸኳይ ውሳኔ በመፈለጉ ውሳኔው ለዩኒቨርሲቲው ድህረ ምረቃ ካውንስል ቀርቦ እንዲጸድቅ የተደረገ መሆኑንና ለወደፊቱ ግን በደንቡ መሰረት መሰራት እንደሚኖርባቸው እና በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው በኩል የሚወጡ የትምህርትና አገልግሎት ዋጋዎች የሚወሰኑት በቦርድ በኩል መሆኑን በተለምዶ የሚያውቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

40. የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በትምህርት ሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው አለማጸደቃቸው እንዲሁም በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማትም አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ አለማሳወቃቸው መንግሥት በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 መሰረት ተቋማቱ ከሀገሪቱ እና ከህዝቡ እድገት አንጻር የትምህርት አገልግሎትን በተመጣጠነ ክፍያ ለማዳረስ የታሰበው ግብ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል አሠራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>**የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ፤**</u>

41. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጁ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

42. በናሙና ተመርጠው በታዩት አራት የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያ ወጥ በሆነ መልኩ ያልተዘጋጀ ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጀው እገዛ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

43. በነዚሁ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢን የሚያሰተዳድር ክፍል መኖሩንና ተጠሪነቱ ሲታይ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሁን ራሱን የቻለ ምክትል ፕሬዝዳንት በስሩ በዳይሬክተር ደረጃ በተቋቋመ አካል እንዲመራ መወሰኑንና ይህ አካል የመተዳደሪያ ደንብና መመሪያ እና መዋቅር በማዘጋጀት ላይ መሆኑን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደ ዩኒቨርሲቲ ገቢዎችን የሚያስተዳድር ክፍል ስላልነበረ እንዲሁም በትምህርት ሚ/ር የሚዘጋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ሲጠበቅ እንደነበረ እና አሁን ባለው ሁኔታ ገቢዎችን የሚመለከት ዳይሬክተር ቢሮ ስለተደራጀ ባለው ሁኔታ ላይ በመመስረት መመሪያ በአጭር ጊዜ ለማዘጋጀት መታቀዱን፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እስከ 2005 በጀት ዓ.ም ድረስ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ በውሳኔ መሰረት እየተፈጸመ የቆየ መሆኑን፤ በአሁኑ ሰዓት መመሪያውን ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጎ መጽደቅ የሚቀረው መሆኑን እና ግኝቱ ትክክለኛ እንደሆነ እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ መመሪያ መዘጋጀት እንዳለበት የሚያምኑ መሆኑን ገልጸው፣ ነገር ግን በእነርሱ በኩል ያልተዘጋጀ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

44. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፋይናንስ መመሪያዎችን፣ የውስጥ ገቢ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ ላይ ይበልጥ መብራራት እንደሚገባቸው ታምኖባቸዋል፤ በመሆኑም ከበጀት አፈቃቀድ፣ ሪፖርት አቀራረብና የሰነዶች አጠቃቀምን አስመልክቶ የተለዩ አንቀጾችን በየሚመለከተው የፋይናንስ መመሪያ እንደሚቀመጥ ገልጸዋል፡፡

45. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ባለማዘጋጀቱ ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጅ እገዛ ባለመደረጉ፣ ውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

እንዳይኖር በማድረግ ከውስጥ ገቢ የሚሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ለአሰራር እና ለቁጥጥር አመቺ እንዳይሆን እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ፤

46. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ በጀት ኮድ ቁጥር 1900 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፀድቆ እና ተመዝግቦ ከተመደበላቸው በጀት በላይ ሊጠቀሙ አይገባም፤ እንዲሁም ገቢውን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የተመደበላቸው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር የማይጣጣም ሲሆን፣ በየወሩም የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ እንደማያዘጋጁ፣ ነገር ግን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህን ያህል በጀት ይጽደቅልኝ ብሎ ገ/ኢ/ል/ሚ/ርን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ከውስጥ ገቢ የተጠቀመውን መጠን ሙሉ በሙሉ የማያሳውቅ እና በሪፖርቱ ውስጥም የማያካትት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ 5 ቀርቧል) ፡፡

48. ስለ ጉዳዩ በናሙና በታዩት የአራቱ ዩኒቨርሲቲዎች የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተጠቃለለውን በጀት ብቻ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ነገር ግን የውስጥ ገቢ ላይ ልምዱ እንደሌለ፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አንዳንድ ክፍተት ስለሚኖር ለወደፊት የሚስተካከል መሆኑን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ችግሩ እቅድ ላይ እንደሆነ እና ለወደፊት በግኝቱ መሰረት እንደሚያስተካክሉ እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ እራሱ በእጅ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ስለሆነ መጠቀም እንጂ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ እንደማያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

49. ከውስጥ ገቢ የሚገኘው የገንዘብ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በበጀት እንዲጸድቅ ሲላክ በዝርዝር ዕቅድ ላይ የተመረኮዘ አለመሆኑ በሁሉም በናሙና በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች የተመደበላቸው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር እንዳይጣጣም አድርጎታል፡፡ እንዲሁም ለውስጥ ገቢ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አለመዘጋጀቱ የመንግስት ገንዘብ ከታቀደለት አላማ ውጪ እንዲውል ሊያደርገው ስለሚችል አሠራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያገኙትን አስፈቅደው የሚጠቀሙ መሆኑን እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ መፈጸሙን በተመለከተ፤</u>

50. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ የሚያገኙት የተለያዩ ገቢዎች አስፈቅደው ሊጠቀሙ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው ሊፈጸሙ ይገባል፡፡

51. በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ስር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያስገኙትን አስፈቅደው የማይጠቀሙ እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው የማይፈጸሙ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁሉም የገቢ ማመንጫ ተቋማት የግዥ ዕቅድ የሌላቸው፣ በመጽሀፍት ማዕከል እና በስድስት ኪሎ ተማሪዎች ክበብ ግዥ ሲፈጽሙ፣ የሁሉም ተጫራቾች መረጃ አለመኖሩ፣ በመጽሀፍት ማዕከሉ ከ2002 ዓ.ም-2005 ዓ.ም የግዥ ኮሚቴ ያልተቀየሩ መሆኑ እና ከአንድ አቅራቢ(ከናጎያ ትሬዲንግ) ብቻ በተደጋጋሚ ግዥ መፈጸሙን፤ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አብዘኞቹ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የግዥ እቅድ የሌላቸው እንዲሁም የግዥ አፈጻጸም መመሪያ የሌላቸው እና የማያውቁት መሆኑን እንዲሁም በሞዴል ፋርማሲ ቁጥር አንድና ሁለት ግዥ በቁጥ ቁጥ የሚፈጽሙ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በአባሪ 6 ዝርዝሩ ተገልጿል፡፡ በባህር ዳር እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ከውስጥ ገቢ በዕቅድ ሳይያዝ ግዥ የሚፈጸም እና የግዥ ዕቅድ ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ የማይቀርብ እንደሆነ በኦዲቱ ለማየት ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት ለሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲዎቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ በፊት በተለምዶ ይሰራ እንደነበረና አንዳንድ አቅርቦቶች ላይ ጥቃቅን በመሆናቸው ተጫራቾች አለማግኘታቸውን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ይህም ቀደም ሲል ከተበታተነ አደረጃጀት የመነጨ ሆኖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግስት የግዥ መመሪያ እንዲጠቀሙ በአማራጭ ገቢዎች ቦርድ ጸድቆ የተዘጋጀ እንደሆነ እና ይኸው ለገቢ ማመንጫዎች ተግባራዊ እንደሚሆን፣ ቁጥ ቁጥ ግዥን አስመልክቶ በደንበኞች የሚፈለጉ መድሃኒቶችን በአስቸኳይ ለማቅረብ እንደሆነ ነገር ግን ከመመሪያ አንጻር ትክክል ስላልሆነ ለወደፊቱ የሚስተካከል እንደሆነ እና በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተለመደ አሰራር አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

53. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያገኙትን አስፈቅደው የማይጠቀሙ እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ የማይፈጽሙ መሆኑ በዕቅድና ከጥቅል ግዥ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ ግዥ መፈጸማቸውን በተመለከተ፤</u>

54. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ የገበያ ጥናት ሊያካሂዱ እና ለግዥ ሰራተኞች የሚሰጠው ቅድመ ክፍያ ጣሪያ ሊወሰን ይገባል፡፡

55. በአዲስ አበባ ፣ጅማ እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማመንጫ ተቋማቱን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ፣ የገበያ ጥናት የማይጠቀሙ እና ለግዥ ሰራተኛ የሚሰጡት ቅድመ ክፍያም በየተቋማቱ ወጥ ያልሆነ እንዲሁም በየገቢው ማመንጫዎች አይነት የተለያየ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲዎቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ፣ ጅማ እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የተደራጀ አሰራር ባለመኖሩ እንዲሁም በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

57. የዋጋ መጋነን ሲታይ የገበያ ጥናትን አለመጠቀም እንዲሁም ለግዥ ሰራተኛ የሚሰጡት ቅድመ ክፍያ ጣሪያ አለመወሰኑ የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ እና ክፍያው ላልተፈለገ ዓላማ እንዲውልና ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ስለሚችል አሠራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የዩኒቨርሲቲዎቹ የውስጥ ገቢ ማመንጫ ተቋማት አደረጃጀትን በተመለከተ፤

58. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡

59. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ እና የአሰራር ሥርዓት ያላቸው ባለመሆናቸው ምክንያት ለተመራቂ ተማሪዎች በየአመቱ በራሳቸው ገቢን እያስተዳደሩ እንዲጠቀሙበት የገቢ ማመንጫዎችን በባለቤትነት እንደሚሰጡ፣ ለግለሰብ ጭምር የገቢ ማመንጫ ተቋማቶቹን በነጻ የሚሰጡ መሆኑ፣ የገቢ ማመንጫ የሥራ ሂደት እያንዳንዱ የገቢ ማመንጫ ያስገኘውን ገቢ ለይቶ አለማወቁ፤ እንዲሁም የገቢ ማመንጫዎቹ ውል ሰጪ በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎች /ሰሻል፣ ግዥ፣ ቤቶች ልማት፣ የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት/ መሆናቸው ታውቋል፡፡ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች አገልግሎት ሥር የሚተዳደሩ ገቢ ማመንጫዎች መኖራቸው፣ በዩኒቨርሲቲው የግብርና ኮሌጁ መዝናኛ ክበባት በኮሚቴ የሚመሩና ከኮሌጁ ፋይናንስ የሥራ ሂደት ጋር ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ የዩኒቨርሲቲው እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የማህበረሰብ ት/ቤቱ በገቢ ማመንጫ ሥር የሚተዳደሩ አለመሆናቸውን ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

60. ስለ ሁኔታው በተቋማቱ የሚገኙ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ በፊት በተደራጀ መልኩ የሚያስተዳድር አካል ባለመኖሩ የተፈጠረ ችግር መሆኑን ፣በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል በየቦታው አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ ስለሆነ በተደራጀ ሁኔታ አለመታቀፋቸውን፤ አሁን ግን ማንኛውም ገቢ የሚያመነጭ ክፍል በገቢ ማመንጫና ኢንቨስትመንት ዳይሬክተር ሥር መተዳደር እንዳለበት በማኔጅመንት የተወሰነ መሆኑን ፣ በባህር ዩኒቨርሲቲ የአደረጃጀት ችግር ያለ መሆኑን እንዲሁም በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል የተቋሙ አወቃቀር በፕሬዝዳንቱ ፍሬም ወርክ

የሚመራ በመሆኑ የተለያዩ የገቢ አይነቶችን በተለያየ አካል ሥር እንዲተዳደሩ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

61. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ አለመሆናቸው ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ እያንዳንዱ የገቢ ማመንጫ ተቋም ለተቋሙ የሰጠውን የአገልግሎት መጠን ወይም ያስገኘውን ትርፍ ለይቶ ለማወቅ እና ተጠያቂነተን ለማጉልበት አዳጋች ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን የሚያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

62. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያሳውቁ፤ ገቢና ወጪን በበጀት ኮድ 1900 ሊመዘግቡ እንዲሁም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አስደርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማያሳውቁ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡትን እና ወጪ ያደረጉትን ሙሉ በሙሉ በበጀት ኮድ 1900 የማይመዘግቡ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

64. ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 140 የገቢ ማመንጫዎች እያሏቸው ሙሉ በሙሉ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያላሳወቁ መሆኑን ፤በጅማ ዩኒቨርሲቲ ብዛታቸው 10 የሆኑ የገቢ ማመንጫዎች እያላቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያላሳወቁ መሆኑን እና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በ2003 እና 2004 ዓ.ም በቅደም ተከተላቸው እንዲጸድቅላቸው ከውስጥ ገቢ የጠየቁት የበጀት መጠን ብር 3,900,000 እና 22,910,100 ሲሆን በዩኒቨርሲቲው በ2003 እና 2004 ዓ.ም የተሰበሰበው

የገንዘብ መጠን ብር 9,410,743 እና ብር 22,504,995.92 መሆኑን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብዛታቸው 7 የሆኑ የገቢ ማመንጫዎች እያላቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያላሳወቁ መሆኑን፣ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በ2003 እና 2004 ዓ.ም በቅደም ተከተላቸው እንዲጸድቅላቸው ከውስጥ ገቢ የጠየቁት የበጀት መጠን ብር 8,765,500 እና 8,766,000 ሲሆን በዩኒቨርሲቲው በ2003 እና 2004 ዓ.ም የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን ብር 35,410,519.16 እና ብር 16,877,751.20 መሆኑን፣ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ብዛታቸው 22 የሆኑ የገቢ ማመንጫዎች እያላቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያላሳወቁ መሆኑን፣ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በ2003 እና 2004 ዓ.ም በቅደም ተከተላቸው እንዲጸድቅላቸው ከውስጥ ገቢ የጠየቁት የበጀት መጠን ብር19,112,400 እና 19,112,500 ሲሆን በዩኒቨርሲቲው በ2003 እና 2004 ዓ.ም የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን ብር 20,834,547.64 እና ብር 23,969,268 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከሚገኙ የገቢ ማመንጫዎች ውጪ ከ 2003 እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ በሌሎቹ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የውስጥ ኦዲት ያልተከናወነ መሆኑን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ከ10 የገቢ ማመንጫዎች በ4ቱ ላይ ብቻ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት ያከናወነ ሲሆን በሌሎቹ ያልተከናወነ መሆኑን፣እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው መጻሐፍትና ሽቀጣ ሽቀጥ ማዕከል የተከናወነው ኦዲት በውስጥ ኦዲተሮች ትርፍ ሰዓት ክፍያ ኦዲት መደረጉን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ2003 -2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በዋናው ግቢ የተከናወነው የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ለፋይናንስ እና ለገቢ ማመንጫው የሥራ ሂደት ተልኮ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን እና በቴክስታይል እና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኦዲት አለመከናወኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

66. በኦዲቱ ወቅት ስለጉዳዩ ለአዲስ አበባ፣ ለጅማ፣ ለባህርዳር እና ለአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰበሰበው ገቢ በየኮሌጁ ስለሆነ ይህን አጠናቅሮ በማዕከል

የተጠቃለለ መረጃ ይዞ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሚያስተላልፍ አካል አለመኖሩን እንዲሁም ከኦዲት ጋር በተያያዘ የአቅም ውስንነት መኖሩን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ጥቂት የገቢ ማመንጫዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማሳወቅ መሞከሩን ሌሎቹን የገቢ ማመንጫዎች ደግሞ የተዘጋጀ መመሪያ ባለመኖሩ የግንዛቤ ችግር መኖሩን እና ኦዲት ያልተከናወነው በሰው ኃይል እጥረት የተከሰተ መሆኑን እንዲሁም በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግኝቱን እንደሚቀበሉት እና ለወደፊት እንደሚያሻሽሉ ገልጸዋል፡፡

67. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አለማሳወቃቸው፤ ገቢና ወጪን በበጀት ኮድ 1900 እንዲመዘግቡ አለመደረጉ እንዲሁም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አስደርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት አለማቅረባቸው እንደዚሁ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሚቀርቡለትን ከመቀበል በአዋጁ መሠረት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤</u>

68. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጉና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን ሊወስዱ ይገባል፡፡

69. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫዎቹን ውል ፈጽመው የተከራዩ ተከራዮች ከውሉ አላማ ውጪ በተጨማሪ ተለጣፊ ሱቅ በመሥራት፣ የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ፣ የኮምፒዩተር አገልግሎት፣ የፑል ጨዋታ አገልግሎት እየሠጡ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥር የሚገኙና በውጭ አካል (Outsource የተደረጉ) አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የገቢ ማመንጫዎች በጨረታ አግባብ ወይም ተጫርተው አሸንፈው እና በዚህም ላይ ተመስርቶ የኮንትራት ውል የተሠጣቸው ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ

ወይም ሰነድ ከፋይላቸው ጋር ያልተያያዘ መሆኑ ታውቆ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ፤ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር አንድ ብር48,055.23 እና በሞዴል ፋርማሲ ቁጥር ሁለት ብር 189,220.92 የሚያወጡ መድሃኒቶች በቁጥ ቁጥ እየተገዙ ጊዜያቸው አልፎ በ30//10/04 የተወገዱ መሆኑን፣ በጅማ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚገኙ እና በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው 107 የዕቃ አይነቶች በአፋጣኝ እንዲወገዱ አለመደረጉ ወይም በግዜያዊ መጠለያ እንዲሰበሰቡ አለመደረጋቸውን፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻና ጥገና ኢንተርፕራይዝ 12 የዕቃ አይነቶች ብዛታቸው 3,163 የገንዘብ ተመናቸው ብር 588,440 የሆኑ ንብረቶች መጠለያ በሌለበት ተከማችተው ለአደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ መኖሩን፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በገቢ ማመንጫው ስር የሚገኘው የከብት እርባታ ከ2003- 2005 ዓ.ም ያሉ የከብቶች ብዛት እንዲሁም በህይወት ያሉና የሞቱ ተለይተው በመረጃነት አለመያዛቸውን፣ በሂሳብ ማረካከቢያ ቅጽ የአስረካቢው ሥምና ፊርማ እንዲሁም የተረካቢው ሥምና ፊርማ የማይመዘገብ መሆኑን እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው በውል የተከራዩ የገቢ ማመንጫዎች በውሉ መሰረት ጊዜውን ጠብቀው ኪራይ እንዲከፍሉ አለመደረጉን እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በዩኒቨርሲቲው የቤት አቅርቦት የተሰጣቸው ሠራተኞች ከውስጥ ገቢ የቤት አበል እየተከፈላቸው መሆኑን፣ በጅማ ከ10 ገቢ ማመንጫ በስድስቱ፣ አዳማ እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች በሁሉም የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከ2003- 2005 ዓ.ም የተገኘውን ትርፍ/ኪሳራ፣ የነበራቸውን የካፒታል መጠን እንዲሁም የወጣው የገንዘብ መጠን አለማወቃቸው እየታወቀ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

70. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት ለሚመለከታቸው የተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክትትል ችግር መኖሩን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ወጥ የሆነ አፈጻጸም መመሪያ አለመኖሩንና የሰው ኃይል ብቃት ችግር መኖሩን ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተቀናጀ የስራ ሂደት አለመኖሩን እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ የአደረጃጀት ችግር መኖሩን ገልጸዋል፡፡

71. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት አለመዘርጋታቸውና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን አለመውሰዳቸው ለብልሹ አሠራር በር የከፈተና ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

<u>በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡና የሙያ ሥነ ምግባር የሚያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤</u>

72. በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ እንዲሁም የሙያ ሥነ-ምግባርን እንዲያውቁ የተደረጉና የሚተገብሩ ሊሆን ይገባል፡፡

73. ሆኖም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ፣ በጅማ፣ በባህር ዳር እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ አለመሆናቸውን እንዲሁም የሙያ የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲያውቁት እና ተግባራዊ እንዲያደርጉት አለመደረጉ ታውቋል፡፡

74. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የአደረጃጀት ችግር መኖሩን እና መመሪያው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያለ ቢሆንም ለገቢ ማመናጫዎች እንዲሰራጭ አለመደረጉን ነገር ግን ለወደፊት እንዲተዋወቁ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

75. በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ አለመሆናችው እንዲሁም የሙያ ሥነ-ምግባርን እንዲያውቁት አለመደረጉ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዳይኖር እና የሥነ ምግባር ችግር እንዲከሰት ከማድረጉም በላይ ብቃት በሌላቸው ሠራተኞች ሥራ ሊሠራ ስለሚችል የስራውን ውጤታማነት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን በተመለከተ፤</u>

76. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

77. ይሁን እንጂ የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ መመሪያ ቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 መሰረት አለመሆኑን እና የውስጥ ቁጥጥርን ለማጠናከር የሚያስችል የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003ን ተግባራዊ አለማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ መመሪያ ቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 መሰረት የሠራተኛውን ደህንነት ጠብቆ የተሟላ የሥራ ውጤት ለማግኘት እንዲቻል አንድን ሰራተኛ በወር ውስጥ እጅግ ቢበዛ ከ60 ሰዓት ትርፍ ሰዓት በላይ ማሰራት እንደማይቻል ይገልጻል፤ ነገር ግን አንዳንድ የገቢ ማመንጫዎች ከተጠቀሰው ሰዓት በላይ አሰርተው የሚከፍሉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው በሰንጠረዥ ተመልክቷል፡-

ተ.ቁ.	የገቢ ማመንጫ ስም	ትርፍ ሰዓት የተከፈለው ሠራተኛ መለያ ቁጥር /ID No./	ትርፍ ሰዓት የተሠራበት ወር	ሠራተኛው ትርፍ ሰዓት የሰራው መጠን	ከተፈቀደው 60 ሰዓት በላይ ልዩነት
1	የመጽሐፍ ማዕከል (Book Center	71336	ሰኔ/2004	84 ሰዓት	24
		71357	ሰኔ/2004	84 "	24
		713	ሰኔ/2004	84 "	24
		71336		84 "	24
		71354	ሰኔ/2004		
		71333	ሰኔ/2004	84 "	24
		መለያ ቁጥሩ ያልታወቀ	መጋቢት/2005	75 "	15
2	በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝ ሆስፒታል ፋርማሲ ክፍል /ከውስጥ ገቢ የተከፈለ/	መለያ ቁጥር የለውም	መጋቢት/2004	80 "	20

79. እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመለያ ቁጥር 71336 የተለያየ ስም ያላቸው 3 ሠራተኞች እያንዳንዳቸው 84 ሰዓት በልዩነት 24 ሰዓት ሠርተው ክፍያ የተፈፀመላቸው፣ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሠሩ የዩኒቨርስቲው ሠራተኞች በማስከፈያ ሊስት ላይ ስለትክክለኛነቱ ያዘጋጀው እና ያረጋገጠው ሠራተኛ ፊርማ የማይሞሉ፣ በሁሉም የገቢ ማመንጫዎች የትርፍ ሰዓት መከታተያና መቆጣጠሪያ ቅጽ በአግባቡ የማይሞላና ሰራተኞቹም በየቀኑ የማይፈርሙ ፤በጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የትርፍ ሰዓት መመሪያን የማያውቁና በተደጋጋሚ የትርፍ ሰዓት ክፍያን የሚፈጽሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

80. የኪራይ ገቢን አሰባሰብን በተመለከተ፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ፤ ዩኒቨርስቲዎቹ በሚፈጽሙት ውል መሠረት የውል ሰነዱ ጊዜው እንዳለቀ ያለ ምንም ተጨማሪ ማስታወቂያ ውል ተቀባይ ከዩንቨርሲቲው የተረከባቸውን አስረክቦ እንደሚለቅ

የተዋዋሉ፣ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደታቻለው አብዛኞቹ ተከራዮች የውል ጊዜያቸውን ማሳለፋቸውን እንዲሁም የዋጋ ተመናቸውም በየጊዜው እየተጠና እንደማይሻሻል እና ተከራዮች ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲከፍሉ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር ሥር ስታፍ ላውንጅ በ1993 ዓ.ም ውል በገቡት መሰረት 1,850 ብር እንዲከፍሉ የተዋዋሉ ቢሆንም ከ1993 ዓ.ም- 2004 ዓ.ም ድረስ ክፍያ ያልፈጸሙ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡-

ተ.ቁ.	የኪራይ ዓይነት	የወር ኪራይ በብር	ውሉ የሚያልቅበት ቀን	ውሉን ያሳለፉበት ጊዜ /በ 2005 ዓ.ም ሲቃኝ/
1	ማለዳ ካፌ /6 ኪሎ በዋናው ግቢ/	3000.00	ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.	10 ወር ከ20 ቀናት
2	የዕጽዋት ውጤቶች መሸጫ ኪዮስክ /አራት ኪሎ የተፈጥሮ ሳይንስ ካምፓስ/	4800.00	በ13/08/2003 ዓ.ም.	2 ዓመት ከ1 ወር
3	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር ሥር ስታፍ ላውንጅ	1850.00	መስከረም 1/1993 ዓ.ም.	12 ዓመት

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡-

ተ.ቁ	የኪራዩ ዓይነት	ኪራይ ያልተከፈለበት ዓ.ም	የተከራይ ሥም	ኪራይ ያልተከፈለባቸው ወራት ብዛት
1.	የወንድ ተማሪዎች ጸጉር ቤት	2004	በሪሁን ገዳሙ	2
2.	የፎቶ ኮፒ ቤት	2004	ኤፍሬም ደሳለኝ	10
3.	የሴት ተማሪዎች የውበት ሳሎን	2004	ዮርዳኖስ ባንቴ	8
4.	የሴት ተማሪዎች የውበት ሳሎን	2005	ዮርዳኖስ ባንቴ	1

81. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በተለያየ አካል የተያዙ በመሆኑ እና በአንድ አካል ባለመተዳደራቸው የተፈጠረ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

82. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ አለመሆናቸው ተቋማቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ በማድረግ የተቋማቱን አቅም ያዳክማል፡፡

<u>የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማቅረባቸውን በተመለከተ፤</u>

83. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው ሊያቀርቡ እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ሂደቶች በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡

84. በናሙና ተመርጠው በታዩት አራቱ ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በአመቱም መጨረሻ የማያቀርቡ መሆኑን እንዲሁም ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ክፍሎች (የፋይናንስ አስተዳደር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር፣ የገቢ ማመንጫ፣ የተከታታይ ትምህርት፣ የተማሪዎች አገልግሎት…) በቅንጅት አለመስራታቸውን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

85. ስለ ጉዳዩ የተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከዚህ በፊት የተደራጀ አሰራር አለመኖሩንና ለወደፊት ለማስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

86. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው አለመቅረባቸው እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ሂደቶች በቅንጅት አለመስራታቸው የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓቱ የላላ መሆኑንና የተጠናከረ ተጠያቂነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ሃሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም፣ ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በናሙና በኦዲቱ ተመርጠው በታዩት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሣቦች ላይ ተደርሷል፡-

87. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን አግባብ ባለው ደረሰኝ እና በተቋሙ ቋሚ ሰራተኛ ሊሰበስቡ እንዲሁም የተሰበሰበውን የውስጥ ገቢ ለመቆጣጠር የሚያስችል ቅጾችን በማዘጋጀት አደራጅተው ሊያስቀምጡ ሲገባ፣ በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 4/አራት/ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡት በኮንትራት ሰራተኞች /የተሚላ ዋስትና በሌላቸው/ ሲሆን፣ የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስችሉ ቅጾችን አለማዘጋጀታቸው፣ እንዲሁም በጅማ ዩኒቨርሲቲ አብዛኛው በዩኒቨርሲቲው ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚጠቀሙት ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ወይም በሚ/ር መ/ቤቱ ፍቃድ በሚዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ አለመሆኑ እንዲሁም የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞቹ ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ የሚያጣራ፣ የሚከታተል እና መዝግቦ የሚይዝ አካል አለመኖሩ፣

88. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ሲገባቸው፣ በአዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ሥር

የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሰበሰቡትን ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ የማያደርጉ መሆኑን እና በጅማና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች የተለያየ የባንክ ቁጥሮች በሚፈልጉት ባንክ ከፍተው የሚጠቀሙ መሆኑ፣ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች በሶስቱ (አዲስ አበባ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚሰበስቡትን ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፣

89. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በትምህርት ሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማጸደቅ ሲኖርባቸው፣ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማትም አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ ሲጠበቅባቸው፣ በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ አራት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (አዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ዩኒቨርሲቲዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥ የመንግሥት የፋይናንስ ደንብ በሚያዘው መሠረት በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው የማያጸድቁ መሆኑ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማትም አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ የተጠያቂነት መርህ በሚጠይቀው መሠረት ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሳያሳውቁ በራሳቸው የሚያከናውኑ መሆኑ፣

90. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ማድረግ ሲገባው፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ዩኒቨርሲቲዎች

የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን አሠራር፣ ክትትልና ቁጥጥር ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ መመሪያዎችን በማስተዋወቅ (awareness) ፣ ስልጠና በመስጠት እና ስለ ውስጥ ገቢ አተገባበር ስርዓት በአካል በመገኘት ሙያዊ እገዛ ያላደረገ መሆኑ፣

91. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ሲኖርበት ያላዘጋጀ ወይም እንዲያዘጋጁ እገዛ ያላደረገ መሆኑ፣

92. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ በጀት ኮድ ቁጥር 1900 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፀድቆ እና ተመዝግቦ በተመደበላቸው በጀት ብቻ መጠቀማቸው፤ እንዲሁም ገቢውን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማቅረባቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ሲገባ፣ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የተመደበላቸው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር የማይጣጣም ሲሆን፣ በየወሩም የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ እንደማያዘጋጁ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህን ያህል በጀት ይጽደቅልን ብለው ገ/ኢ/ል/ሚ/ርን የሚጠይቁ ቢሆንም፣ ከውስጥ ገቢ የተጠቀሙትን መጠን ሙሉ በሙሉ የማያሳውቁ እና በሪፖርታቸው ውስጥም የማያካትቱ መሆኑ፣

93. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ከተለያዩ ምንጮች ያገኙትን ገቢ አስፈቅደው ሊጠቀሙ እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን መከተል ሲኖርባቸው፣ በአዲስ አበባ ፣ በጅማ ፣ በባህር ዳር እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ስር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያስገኙትን አስፈቅደው የማይጠቀሙ እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው የማይፈጸሙ መሆኑ፣

94. የመንግሥት የግዥ መመሪያ በሚያዘው መሠረት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ፣ ተቋማቱ የገበያ ጥናት ሊጠቀሙ እና ለግዥ ሰራተኛ የሚሰጠውን ቅድመ ክፍያ ጣሪያ መወሰን ሲኖርባቸው፣ በአዲስ አበባ፣ ጅማ እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ የገበያ ጥናት የማይጠቀሙ እና ለግዥ ሰራተኛ የሚሰጡት ቅድመ ክፍያም ወጥ ያልሆነ እንዲሁም በየገቢው ማመንጫዎች አይነት የሚሰጠው መጠን የተለያየ መሆኑ፣

95. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ የሚሰበስቡ ድርጅቶች ለአሠራር ቅንጅትና ከተጠያቂነት አንፃር በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ ተጠሪነታቸው በታወቀ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ ሊሆኑ ሲገባቸው በናሙና ተመርጠው በታዩት አራቱ ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የመዋቅር ጥናት የሌላቸው እና በተለያየ መምሪያ ሥር ተጠሪ ሆነው የሚተዳደሩ መሆኑ፣

96. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያሳውቁ፤ ገቢና ወጪን በበጀት ኮድ 1900 ሊመዘግቡ እንዲሁም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አስደርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ ሲኖርባቸው፣ በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማያሳውቁ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡትን እና ወጪ ያደረጉትን ሙሉ በሙሉ በበጀት ኮድ 1900 የማይመዘግቡ መሆኑ እና በአብዛኛዎቹ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከ2003-2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ኦዲት አለመከናወኑ፣

97. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጉና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን ሊወስዱ ሲገባቸው፣ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና

አጠቃቀም እና ክትትል ቁጥጥር ሥርዓትን ያልዘረጉና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን የማይወስዱ መሆኑ፣

98. በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሠረት የተመደቡ እንዲሁም የሙያ ሥነ ምግባርን የሚያውቁትና የሚተገብሩ ሊሆኑ ሲገባቸው፣ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሠሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ አለመሆናቸው፤ እንዲሁም የሙያ ሥነ-ምግባርን መርህና ግደታምችን የማያውቁትና የማይተገብሩት መሆኑ፣

99. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያን መከተል ሲገባቸው፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) የውስጥ ቁጥጥርን ለማጠናከር የሚያስችል የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003ን ከተከራዮች ጋር ውል በተገባው መሠረት ተግባራዊ አለማድረጋቸውን እና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ መመሪያ ቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 መሰረት መከፈል በሚገባው መጠን ብቻ አለመሆኑ፣

100. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው ሊያቀርቡ እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ሂደቶች በቅንጅት ሊሰሩ ሲገባቸው፣ በናሙና ተመርጠው በታዩት አራቱ ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት የተጠያቂነት መርህ መሠረት፣ ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በአመቱም መጨረሻ የማያቀርቡ መሆኑ፣ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ክፍሎች (የፋይናንስ

አስተዳደር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር፣ የገቢ ማመንጫ፣ የተከታታይ ትምህርት፣ የተማሪዎች አገልግሎት...) በቅንጅት የማይሠሩ መሆኑ፣

101. በአጠቃላይ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር መ/ቤት እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ ያለውን ሁኔታ ለማሻሻል ጥረት ማድረግ የሚገባቸው መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ አለመዘጋጀቱ እንዲሁም ወጥ የሆነ ሥርዓት አለመዘርጋቱ የውስጥ ገቢን ለመቆጣጠር እና ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሙያዊ እገዛ አለማድረጉ ተቋማቱ ሚናቸውን በአግባቡ እንዳይወጡት ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲሁም የተጠያቂነት ሥርዓት አለመኖሩና በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ ኦዲት አለመከናወኑ የተሰበሰበው ገቢ በሙሉ በትክክል፣ ለታለመለት ዓላማ ለማዋሉ አለመረጋገጡን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተገለጹት ድክመቶችና ግድፈቶች በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ፤ በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

102. የተሰበሰበውን ገቢ ለመከታተልና ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ እንዲቻል የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን ሲሰበስቡ፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባሳተመው ወይም ገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንዲታተም በፈቀደው ተከታታይ ቁጥር ባለው ደረሰኝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ እንዲሁም በትምህርት ተቋሙ ቋሚ ሰራተኛ እና በየዕለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

103. የመንግስት ገንዘብ ለብክነት እንዳይዳረግ እና ለታለመለት ዓላማ ሥራ ላይ እንዲውል የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደ የባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ሊያደርጉና ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

104. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

105. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጁ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

106. የውስጥ ገቢን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዝርዝር ዕቅድ ላይ ተመረኮዘው የውስጥ ገቢ በጀት በኮድ ቁጥር 1900 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር አቅርበው ሊያፀድቁ እና

የተመደበላቸውን በጀት ከአጠቃቀሙ ጋር አጣጥመው ሊጠቀሙ፤ እንዲሁም ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

107. የውስጥ ክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን እና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያገኙትን አስፈቅደው ሊጠቀሙ እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ ሊፈጸሙ ይገባል፡፡

108. ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ እና እያንዳንዱ የገቢ ማመንጫ ተቋም ለተቋሙ የሰጠውን የአገልግሎት መጠን ወይም ያስገኘውን ትርፍ ለይቶ ለማወቅ ይቻል ዘንድ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡

109. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር እና ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያሳውቁ፤ ገቢና ወጪን በበጀት ኮድ 1900 ሊመዘግቡ እንዲሁም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አድርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

110. የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓቱ የተጠናከረ እንዲሆን የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጉና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ በወቅቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃዎችን ሊወስዱ ይገባል፡፡

111. የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እና ስራው ውጤታማ እንዲሆን በውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ የሚሰሩ

ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሠረት የተመደቡ እንዲሁም የሙያ ሥነ ምግባር መርህን የሚያውቁትና የሚተገብሩ ሊሆን ይገባል፡፡

112. ተቋማቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ ለማድረግ እና የተቋማቱን አቅም ለመገንባት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የተቋማቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ ተገቢ ውልና የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

113. የተጠያቂነትን ሥርዓት ለማጠናከር የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው ሊያቀርቡ እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ሂደቶች በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን እና ለኦዲቱ የሚፈለጉ ቁሳቁሶችን በሙሉ በማቅረብ እንዲሁም ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ- 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue)	የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን 648/2001፣ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም አዋጅ ቁጥር 650/2001 እናየፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 መሰረት ያደረገ መሆኑን ማጣራት፤	1. በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ሊሰበሰብ የሚችለው ተከታታይ ቁጥር ባለውና ሚ/ሩ ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ በሚዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ሊሆን ይገባል፡፡
	2. የመንግሥት ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመሰብሰብ የሚቻለው በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና በተሰጠው ቋሚ የተቋሙ ሠራተኛ ብቻ መሆን አለበት፡፡
	3. የመንግሥት ገንዘብ የሚሰበስበው ሰው በየዕለቱ የሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በየቀኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
	4. ማንኛውም በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ወይም በመ/ቤቱ ስም ወደ ተከፈተው የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሣብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡
	5. የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመንግሥት ተቋም የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	6. የገቢ ማሰባሰቢያ እና የተሰራባቸው የወጪ ማስረጃዎች ወደ ሰነድ ክፍል ተመልሰው በየክፍሉ በአግባቡ ሊያዙ እና ሰነዶቹም ለሥራና ለምርመራ በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉ መልኩ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
	7. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፍቃድ ሳያገኝ ለውስጥ ገቢ ማመንጫ የባንክ ሂሳብ አካውንት ቁጥር ሊከፍት አይገባም፡፡

	8.በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማፀደቅ ይኖርባቸዋል፡፡
	9.የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተፈቀደላቸው የሥራ ዘርፍ አገልግሎትን በሚሰጡበት ወቅት መሰብሰብ ያለበትን የአገልግሎት ገቢ ወቅቱን ጠብቀው ሙሉ በሙሉ ሊሰበስቡ ይገባል፡፡
	10.የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሰበስቡትን የውስጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
2. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ የሚሰበስቡትን የመንግሥት ሀብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ለጸደቀ አላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን እና ውጤታማነን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን ማጣራት፤	11.የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ለመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ወጥ በሆነ መልኩ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	12.የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	13.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ በጀት ኮድ ቁጥር 1900 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፀድቆ እና ተመዝግቦ ከተመደበላቸው በጀት በላይ ሊጠቀሙ አይገባም፡፡
	14.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚያከናውኑዋቸው ሥራዎች የተፈቀደላቸውን አመታዊ የውስጥ ገቢ በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ርማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
	15.ገቢውን ያገኘው የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በገቢው መጠቀም ካልተፈቀደለት በቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡
	16.በዩኒቨርሲቲዎች በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ ሊፈጸም ይገባል፡፡
	17.በበጀት ዓመቱ በከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት ለግዥ ሰራተኞች የሚሰጥ ቅድመ ክፍያ

	ጣሪያ ሊወሰን ይገባል፡፡
	18.የከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማትን ጥቅም ከማስክበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ የገቢያ ጥናት መረጃ መጠቀም ይገባል፡፡
	19.የከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት ባልተፈቀደ የወጪ ርዕስ ከውስጥ ገቢ ክፍያ ሊፈፅሙ አይገባም፡፡
	20.በዩኒቨርሲቲዎች ለውስጥ ገቢ የሆኑ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ ፤የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ ሊሆን ይገባል፡፡
3. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓታቸውን እና የሚያገኟውን የውስጥ ገቢዎች ሙሉ በሙሉ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሚያሳውቁ መሆኑን ማጣራት፤	21.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለውስጥ ገቢ የሚሰበስቡባቸውን ምንጮች፣ ብዛት እና የሚያገኟቸውን ገቢዎች ሙሉ በሙሉ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማሳወቅ ይገባቸዋል፡፡
	22.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ እና ወጪ ሪፖርታቸውን በበጀት /ኮድ ቁጥር 1900/ ከአፈጻጸሙ ጋር በማነጻጸር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡
	23.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ እና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡
	24.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብን እና አጠቃቀምን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግተው ሊጠቀሙ ይገባል፡፡
	25.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም የውስጥ ቁጥጥር ላይ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ አግባብነት በሌላቸው፣ በአሰራር የሚታዩ ችግሮች ላይ ወቅታዊና ተገቢ እርምጃ መወሰድ ይገባቸዋል፡፡
	26.የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡
	27.የማጭበርበር ወይም የስህተት ስጋቶችን ለመቀነስ በአንድ ሰው በመከናወናቸው ምክንያት ለጥፋትና ለስነ ምግባር ችግር ሊጋለጡ የሚችሉ ስራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች መሰራት አለበቸው፡፡(segregation of duties)

	28. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞ ለኦዲተሮች እና ለሂሳብ አዋቂዎች የተዘጋጀ የሥነ ምግባር መመሪያን ሊከተሉ ይገባል፡፡
	29. ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለሙያዎች በመዋቅሩ መሰረት የተሟሉና የትምህርት ደረጃቸውም ቦታው የሚጠይቀው ሊሆን ይገባል፡፡
	30. በከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመንግሥት መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡
	31. የመንግስት ከፍተኛ መንግስት ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው ሊያቀርቡ እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ሂደቶች በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡

አባሪ 2

ተ.ቁ	የገቢው ማመንጫ አይነት	የሚጠቀመው የደረሰኝ አይነት	ደረሰኙ የታተመበት	ደረሰኙ እንዲታተም	ደረሰኙ ተከታታይ ቁጥር ያለው

			ቦታ	የፈቀደው አካል	ሥለ መሆኑ ያረጋገጠው ክፍል/አካል
1.	ሞዴል ፋርማሲ 1 እና 2	Jimma model Pharmacy sales ticket	ጅማ	መረጃ አልተገኘም	ኦዲት
2.	የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች መዝናኛ ክበብ	Jimma University staff launch bar and restaurant reciept	ጅማ	መረጃ አልተገኘም	የለም
3.	የዩኒቨርሲቲው መጻኃፍትና ሸቀጣሸቀጥ ማዕከል	Jimma University book center receipt	ጅማ	መረጃ አልተገኘም	የለም
4.	የጅማ ዩኒቨርሲቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	MOFED	አዲስ አበባ	ገ/ኢ/ል/ሚ/ር	የሆስፒታሉ እስቶር ክፍል
5.	የጅማ ዩኒቨርሲቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መዝናኛ ክበብ	Jimma university specialized hospital staff launch reciept	ጅማ	ሆስፒታሉ	የለም

6.	የጅማ ዩኒቨርሲቲ ቁሳቁስ ማምረቻ ኢንተርፕራይዝ	Jimma University Furniture Production and maintenance enterprise cash receipt voucher	ጅማ	ዩኒቨርሲቲው	የለም
7.	የኪቶ ፉርዲሳ ሁለገብ ልማት ድርጅት	Kito Furdisa receipt voucher	ጅማ	ዩኒቨርሲቲው	በገቢ ማመንጫ ተቋሙ የሚመዘገብ
8.	የጅማ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ	MOFED	አዲስ አበባ	ገ/ኢ/ል/ሚ/ር	የኮሌጁ እስቶር ክፍል
9.	የማህበረሰብ ት/ቤት/community school/	Jimma University community school cash reciept	ጅማ	-	የት/ቤቱ እስቶር ክፍል

አባሪ 3

ተ.ቁ.	የገቢው ማመንጫው ዓይነት	የከፈቷቸው የባንክ ቁጥሮች	የተከፈተው የአካውንት ዓይነት	በአካውንቱ ያለው የገንዘብ መጠን	የባንኩ ዓይነት	ቀን	የባንክ ቁጥር እንዲከፈት ያዘዘው አካል	መግለጫ
ሀ. ጅማ ዩኒቨርሲቲ								
1	ሞዴል ፋርማሲ 1	11630	ከረንት አካውንትና ሴቪንግ አካውንት	8,426,821.27	አቢሲኒያ	30/01/13	-	
		…033	ከረንት አካውንት	-	አቢሲኒያ	-	-	የተዘጋ
		..043	ስፔሻል ሴቪንግ አካውንት	5,029.59	“	21/01/13		
		1000035049596	-	1,411,971.10	የኢትዮጵያ ንግድ	26/02/13	ዩኒቨርሲቲው	
2	ሞዴል ፋርማሲ 2	11631	ሴቪንግ አካውንት	424,864.42	አቢሲኒያ	30/01/13	-	
		…106	ከረንት አካውነት	-	“	-	-	የተዘጋ
		…044	ስፔሻል ሴቪንግ አካውንት	1,666.02	“	21/01/13	-	
3	የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች መዝናኛ ክበብ	…32778	ሴቪንግ አካውንት	140,497.19	የኢትዮጵያ ንግድ	19/07/12	-	
		1000018483134	ከረንት አካውንት	991,297.32	የኢትዮጵያ ንግድ	31/01/13	-	
4	የዩኒቨርሲቲው መጽሐፍትና ሽቀጣ ሸቀጥ ማዕከል	1000018487393	ከረንት አካውንት	137,796.66	የኢትዮጵያ ንግድ	12/01/13	-	

5	የጅማ ዩኒቨርሲቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መዝናኛ ክበብ	1000024540239	ሴቪንግ አካውንት	147,973.78	የኢትዮጵያ ንግድ	26/02/13	ሆስፒታሉ	
6	የጅማ ዩኒቨርሲቲ ቁሳቁስ ማምረቻ ኢንተርፕራይዝ	3121	ሴቪንግ አካውንት	2,700,708.22	ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል	21/02/13	ዩኒቨርሲቲ	
		1000018471632	ከረንት አካውንት	3,526,941.26	የኢትዮጵያ ንግድ	31/01/13	ዩኒቨርሲቲ	
7	የኪቶ ፉርዲሣ ሁለገብ ልማት ድርጅት	C01000018499332	ሴቪንግ አካውንት	24,509,723.41	የኢትዮጵያ ንግድ	31/01/13	-	
8	የማህበረሰብ ትምህርት ቤት /community school/	5021001008007	ሴቪንግ አካውንት	7,728,746.14	ዳሽን	22/02/13	-	
9.	የጅማ ግብርና ኮሌጅ የሰራተኛ መዝናኛ ክበብ	V066501006784	ሴቪንግ አካውንት	604,223.78	የኢትዮጵያ ንግድ	22/11/12	-	
	ድምር			50,758,260.16				

ለ. ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ተ.ቁ.	ገቢውን ያመነጨው አካል	የከፈቷቸው የባንክ ቁጥሮች	የተከፈተው የአካውንት ዓይነት	በአካውንቱ ያለው የገንዘብ መጠን	የባንኩ ዓይነት	ቀን	የባንክ ቁጥር እንዲከፈት ያዘዘው አካል
1		1000033066922	ሴቪንግ አካውንት	37,062.63	የኢትዮጵያ ንግድ	16/03/13	የተማሪዎች

	የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት በጋራ						አገልግሎት
2	የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት በጋራ	1000033809305	ሴቪንግ አካውንት	25,643.9	የኢትዮጵያ ንግድ	27/03/13	የተማሪዎች አገልግሎት
3	የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት በጋራ	1000032899629	ሴቪንግ አካውንት	86,562.02	የኢትዮጵያ ንግድ	27/03/13	የተማሪዎች አገልግሎት
4	የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት በጋራ	1000032950737	ሴቪንግ አካውንት	153,570.01	የኢትዮጵያ ንግድ	27/03/13	የተማሪዎች አገልግሎት
5.	የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት በጋራ	1000034048006	ሴቪንግ አካውንት	115,946.54	የኢትዮጵያ ንግድ	13/03/13	የተማሪዎች አገልግሎት
	ድምር			418,785.10		-	የተማሪዎች አገልግሎት

አባሪ 4

ተ.ቁ	የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን በብር	ገንዘቡ የተሰበሰበበት ቀን	ገንዘቡ ወደ ባንክ ገቢ የተደረገበት ቀን እና ዓ.ም	ገንዘቡ በገንዘብ ሰብሳቢ እጅ የቆየበት ቀን ብዛት
1. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ				
1.	407,456	ከ13/08/2003 - 17/08/2003	በ24/08/2003	12
2.	183,629.30	ከ29/09/2003 - 02/10/2003	በ06/10/2003	8
3	230,852	ከ25/08/2004 - 01/09/2004	በ08/09/2004	14
4	102,528.53	ከ11/08/2004 - 15/08/2004	በ22/08/2004	12
5.	366,458	ከ11/08/2005 - 13/08/2005	በ24/08/2005	13
2. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ				
1.	35,775	ከ17/08/2003 - 11/09/2003	በ11/09/2003	25
2.	8,662	ከ19/08/2003	በ12/09/2003	23

		- 12/09/2003		
3.	20,423	ከ02/09/2003 - 15/09/2003	በ15/09/2003	14
4.	13,506.20	ከ30/08/2004 - 16/09/2004	በ16/09/2004	17
5.	8,803	ከ10/03/2005 - 24/03/2005	በ24/03/2005	15
3. በአዳማ ዩኒቨርሲቲ				
1.	133,309	ከ04/02/2003 - 11/02/2003	በ11/02/2003	8
2.	76,051	ከ12/02/2003 - 15/02/2003	በ15/02/2003	4
3.	21,734	ከ26/02/2003 - 29/02/2003	በ29/02/2003	4

አባሪ 5

ተ.ቁ	የዩኒቨርሲቲው ሥም	ከውስጥ ገቢ የጸደቀ በጀት በብር		ከውስጥ ገቢ ጥቅም ላይ የዋለ በብር		ልዩነት በብር	
		2003 ዓ.ም	2004 ዓ.ም	2003 ዓ.ም	2004 ዓ.ም	2003 ዓ.ም	2004 ዓ.ም
1.	አዲስ አበባ	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም
2.	ጅማ	300,000	19,415,100	357,300	370,100	57,300	(19,045,000)
3.	ባህር ዳር	5,405,500	10,266,000	497,900	5,415,508.66	4,907,600	4,850,491.34
4.	አዳማ	19,112,400	19,112,500	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም	መረጃ ማግኘት አልተቻለም

ማስታወሻ፡- ከላይ የተጠቀሰው ጥቅም ላይ የዋለ የብር መጠን በዩኒቨርሲቲዎች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተዘጋጅቶ የተላከውን ሪፖርት የሚያመለክት ሲሆን፤ ሁሉንም የውስጥ ገቢ አፈጻጸም (ወጪን) ያካተተ አይደለም፡፡ አጠቃላይ ወጪያቸውን የሚያሳይ መረጃ በሁሉም ከላይ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡

ተ.ቁ	የሻጭ ስም	ግዥ የተከናወነበት ቀን	የተከፈለ የብር መጠን (በተደጋጋሚ)
1	ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ	14/11/12	2,807.20
			2,980.40
			2,958.40
			1,444.80
		15/11/12	2,961.90
			2,869.02
			2,231.46
2	ሸነን ጊቤ	19/01/11	2,959
			2,959
			2,959
			2,985.40
			2,959
			1,702.80
		21/01/11	2,977.65
			2,943.10
			2,972.16
3.	ባደርግ ፕራይቬት ሊሚትድ	06/03/05	2,796.50
			1,320
		7/03/05	2,728
			2,440
		8/03/05	2,960